**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!**

# ግበበ ምድር

## ትእይንት አንድ

*/መጋረጃ ሲከፈት ልዕልት እሌኒ መድረኩ ዳር ላይ እንደቆመች ተላላኪ ጠጋ ብሎ ራሱን ወደ እርሷ ሲያስጠጋ …/*

**እሌኒ፡-** ዘወር በል እኮ ነው  የምልህ

**ተላላኪ፡-** ልዕልት እሌኒ ነገሩ የገባሽ አይመስለኝም

**እሌኒ፡-** ብዙ የሚያወራልኝ ሰው አልወድም

**ተላላኪ፡-** በአጭሩ ልናገርና መልዕክቴን ላድርስ

**እሌኒ፡-** እኮ ቶሎ በል

**ተላላኪ፡-** በንጉሥ ኔሮን ትእዛዝ መሠረት እምቢ አንገዛም ያሉ እስራኤላውያንን ለማንበርከክ ከተላኩት ከጋላስ ወታደሮች አለቆች ማለትም ሹማምንቶች…..

**እሌኒ፡-** ባክህ ብዙ አታውራብኝ

**ተላላኪ፡-** እሺ የእኔ እመቤት፤ መልዕክቱ እኮ ከሹማምንቶች ነው የመጣው

**እሌኒ፡-** ምን የሚል?

**ተላላኪ፡-** አንቺን ንጉሥ ኔሮን ባይወልዱሽም ተንከባክበው ስላሳደጉሽና የቅርብ ዝምድና ስላላችሁ ልክ እንደ ልጃቸው ነው የሚያዩሽ

**እሌኒ፡-** መች እሱ ጠፋኝ

**ተላላኪ፡-** እና…እና የላከኝ ሰው አንቺን ለጋብቻ …!

**እሌኒ፡-** ምን (በጩኸትና በድንጋጤ)

**ተላላኪ፡-** ማለት ገና በታላላቅ ሰዎች ነው ቃልኪዳኑ የሚጸናው፡፡ እኔ …

**እሌኒ፡-** እኔኮ ክርስቲያን ነኝ

**ተላላኪ፡-** ልዕልት ዕሌኒ አንቺና ቀውላጦስ በንጉሥ ኔሮን ሹማምንት እንድትጠረጠሩ ያደረገው ይሄው ነው፡፡

**እሌኒ፡-** ምኑ?

**ተላላኪ፡-** ንጉሥ ኔሮንም ሆኑ ሹማምንቶች ክርስቲያኖችን አይወዱም እናንተ ግን ታቀርቡዋቸዋላችሁ ይባላል፡፡ ሌላም…

**እሌኒ፡-** ጨርሰው! ልምን ትደብቀዋለህ ጨርሰው!

**ተላላኪ፡-** ሁለታችሁም ትታማላችሁ

**እሌኒ፡-** የሥጋ ዝምድና ስለሌለን

**ተላላኪ፡-** እሱ እኮ ነው ችግሩ … የተላኩበትን ምን ልበል?

**እሌኒ፡-** ዝም

**ተላላኪ፡-** እንዴት ዝም

**እሌኒ፡** ሀሳቡን ሳነሣባት ዝም አለች ብለህ ዝም በል፡፡

(ተላላኪ ዝም ብሎ ቆሞ ያያታል)

**እሌኒ፡-** አልሰማኸኝም?

**ተላላኪ፡-** እሺ የእኔ እመቤት /እጅ ነሥቶ ይወጣል/

(እሌኒ መጽሐፍ ታነባለች በመሐል ቀውላጦስ ይገባል)

**ቀውላጦስ፡-** እሌኒ

**እሌኒ፡-** አቤት ቀውላጦስ

**ቀውላጦ፡-** ሥራ ይዘሻል?

**እሌኒ፡-** መጽሐፍ ነው የማነበው፤ ባለፈው ክርስቲያኖች ሲያስተምሩ ሥራ መፍታት ለኃጢአት ይዳርጋል ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ገነት መኖሪያ ብቻ ሳትሆን መቅደስም ነበረች፤ ሦስት በሮች ነበሯት በምሥራቅ የእግዚአብሔር መውጫ፣ በሰሜን የአዳም መግቢያ፣ በደቡብ የሔዋን መግቢያ ነበር፡፡ ታዲያ እሌኒ በዚህ ቦታ ነበር ሔዋን መጸለይ ትታ ካልሆነ ጓደኛ ጋር ስታወራ ሰይጣን ያሳታት …

**እሌኒ፡-** ቀውላጦስ ሰሞኑን ከክርስቲያኖች አልሄድክም?

**ቀውላጦስ፡-** ሄጃለሁ የሰሞኑን ደግሞ በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ የሐዋርያት አለቃ የተባለው ጴጥሮስ አስተማረ

**እሌኒ፡-** ከዓሣ አጥማጅነት ሰውን የምታጠምድ ሁን የተባለውና በኋላም የመንግሥተ ሰማያት መክደቻ ቁልፍ የተሰጠው?

**ቀውላጦስ፡-** አውቀሽዋል፤ ይህን ድንቅ የሆነ ቃል የጌታን ልደት፣ መከራ መቀበል፣ ለሰው ልጆች ያደረገውን ድንቅ ሥራ ሲያስተምር … መራራ ቆሻሻ ሕይወትን ይለውጣል፣ ጠማማ ሃሳብን ይቀይራል፣ ለሰው ልጆች ፍጹም ሰላምን መተሳሰብን የሚሰጥ ቃል ተናገረ…

**እሌኒ፡-** በጣም ነው የሚገርመው አብረው ይበላሉ፣ አብረው ይጸልያሉ ነው የሚባለው ሴትም ወንድም እንቅልፍ አያንበረክካቸውም ሲባል ሰምቻለሁ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** በጣም ጎበዝ ናቸው፤ ዝማሬያቸው ራሱ ወንጌል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን እናት ስሟ ሲጠሩ የሄዋን የአዳም ካሣ የተከፈለባት፣ ጥንተ አብሶ ፍርሀት ሞት ድል የተነሣባት፣ መርገመ ሔዋን መርገመ አዳም የተሻረባት፣ የነፍስ መድኃኒት የሕይወት ምግብ ያስገኘች፣ ሰውና እግዚአብሔር የታረቀባት፣ መሠረተ ድኅነት የሰላም አዳራሽ፣ የወንጌል መቅረዝ ናት፤ ሲሉ አቤት! አቤት! ደስ ሲሉ!

**እሌኒ፡-** የእሷን ነገር ሲያነሱማ በጣም ይገርማል፣ ቅድመ ፀኒስ፣ ጊዜ ፀኒስ፣ ድኅረ ፀኒስ ድንግል፤ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል፤ ድንግል በሥጋ ድንግል በኅሊና፣ እናትነትን ከድንግልና ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራ የተገኘች፣ ለሰው ሁሉ ምሕረት፣ የምትለምን አዛኝ እናት፡፡

**ቀውላጦስ፡-** እሌኒ ታዲያ በእኒህ እውነተኛውን ቃል የሚያስተምሩ ሰዎች ንጉሥ ኔሮን እኔን እንዲያመልኩ እኔ በሠራሁት ጣዖት እንዲሰግዱ ብለዋል፡፡ ይህን ካላደረጉ ደግሞ ከባድ ትእዛዝ አስተላልፋለሁ እያሉ ናቸው፡፡

**እሌኒ፡-** ታዲያ ምን እናድርግ የሚታይህ የመፍትሄ ሀሳብ አለ?

**ቀውላጦስ፡-** አንቺ ለንጉሥ ኔሮን የቅርብ ዘመድ ነሽ፡፡ ስላሳደጉሽም የክብር ቦታ ሊያስቀምጡሽ አስበዋል፡፡ እና በተለያየ መንገድ ብለሽ ሀሳባቸውን እንዲያለዝቡ ብታደርጊስ?

**እሌኒ፡-** የሚሰሙኝ አይመስለኝም፤ እኔ ግን እናገራለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ክርስቲያኖችን በገንዘብና ምግብ በመስጠት የአቅሜን ለመርዳት አስቤያለሁ፡፡

**ቀወላጦስ፡-** እሱም ቢሆን በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው፡፡ ከንጉሡ ዘበኞችም አንዱ ክርስቲያን ሆኗል፡፡ እሱንም በመላክ ብዙ ሥራ መሥራት ትችያለሽ፡፡ እኔ ግን ልሂድ /እያለ ይወጣል/

**እሌኒ፡-** (እየተከተለችው) ቀውላጦስ አንድ ነገር ግን ማድረግን አትርሳ፡፡ እኔ የምውለው ቤት ውስጥ ነው እና አንተ የምትማረውን እንድታስተምረኝ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** እሺ. (መጋረጃው ይዘጋል)

**ትእይንት ሁለት**

(መጋረጃ ሲከፈት የንጉሥ መቀመጫ ተስተካክሎ የሁለት አማካሪዎች ወንበር አለ)

**ሠራተኛ፡-** (ትገባና ዘወር ዘወር ብላ እያየች እንደመሳቅ እያለች) ወይ ደስ ሲል! (ደረቷን እየደቃች) አሁን ንጉሥ ሲመጡ እንዲህ ተሰናድቶ ሲያገኙት በጣም ነው ደስ የሚላቸው፡፡ ልዕልት እሌኒ ከብዙ ሴቶች መሐል

መርጣ እንዳስገባችኝ በትክክል በዚህ ከቀጠልኩ ንጉሥ ኔሮንም በጣም ትልቅ ሥልጣን እንደሚሰጡኝ አልጠራጠርም። (ብላ ዘላ ወደ ጓዳ ትገባለች)

**ንጉሥ፡-** ሀገራችን ሮማ የናዝሬቱ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት በ753 ዓ.ዓ የተቆረቆረች፣ ግዛታችን ከእንግሊዝ አንሥቶ እስራኤልን፣ ኤፌሶንን በመጨመር እስከ አረብ ድረስ ዘልቆ ሰሜን አፍሪካን አጠቃሎ ታናሿ እስያን የሚጨምር በጣም ሰፊ ነው አዘገዛዛችን ፍርድን ሳናዛባ በሰላም የምናስተዳደር ሕዝባችን የጠንካራዎች ጠንካራ ከመባሉም በላይ በጀግንነቱ ዓለም የመሰከረለት ነው። በከተማችን ብቻ አንድ ሚሊዮን ነዋሪዎች በደስታና በፈንጠዝያ የሚኖሩባት ናት።

**አማካሪ 1 ፡-** (ብድግ ብሎ እጅ ለመንሣት እንደቆመ) ንጉሥ ኔሮን እርግጥ ነው ያሉት ሁሉ እውነት ነው ዳሩ…

**ንጉሥ፡-** ጀምረህ ተውከውሳ ጨርሰው እንጂ

**አማካሪ 1 ፡-** ዳሩ ይህን ዕውቅ ግዛት የሚያንቀሳቅሰውን የቄሳርን በትረ ሥልጣን የሚንቁ ክርስቲያኖች ናቸው ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ፡-** (በእርጋታ) ያስተዋልኩትን ልብ ብለኸዋል ሁሉን ነገር እናደርጋለን ስገዱልን፣ አምልኩን፣ እኛ ለእናንተ እናንተ ለእኛ ሁኑ አልን እነሱ ግን እነ ቀበጤ እ-ም-ቢ አሉ (በንቀት)

**አማካሪ 2 ፡-** (ብድግ ብሎ እጅ ከነሣ በኋላ ይቀመጥና) በታላቁ ሮም ግዛት ውስጥ ረሀብ፣ ቸነፈር፣ የመሬት መንቀጥቀጥና እነዚህንና የመሳሰሉት መጥፎ ነገሮች በከሀዲ ክርስቲያኖች ምክንያት የሮማ አማልክት ተቆጥተው ያወረዱብን ቅጣቶች መሆናቸውንስ ተረድታችሁት ይሆን?

**አማካሪ 1፡-** እንዴታ በሚገባ ነዋ!

**ንጉሥ፡-** ከዚያም በላይ

**አማካሪ 1፡-** ከዚያም በላይ የሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት፣ ለማስደሰት፣ ለማዝናናት በሚዘጋጁ ቦታዎች ዕፁብ ድንቅ የሆነው ቲያትር በሚታይበት አዳራሽ ክርስቲያኖች ሕገ-ወጥ ነው ብለው አንገባም አሉ። ሰዎችና ሰዎች፣ አውሬዎች ሲታገሉ፣ ሰዎችና ሰዎች ተዋግተው ጀግንነታቸውን ጉልበታቸውን ሲፈትሹ ብሎም የማጥቃት ጥበባቸውን በግልጽ ሲታይ፣ የተራብ እንስሳ የታሰረን ሰው ሲዘነጣጥለው የሚያሳየውን ትርኢት የሚንቁ ንቀውም የሚያስንቁ ክርስቲያኖች ናቸው ንጉሥ ሆይ።

**ንጉሥ፡-** አስገራሚ ፍጡሮች። የሮማን አማልክቱን ናቁ! ለእኛና ለጣዖቶቻችን አንሰግድም አንበረከክም አሉ!

**አማካሪ 2 ፡-** ፍጥነታቸው ነው ያስገረመኝ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው በተባለ ዕለት በአንድ ቀን ከተለያየ ቦታ የመጡ የሐዋርያት አለቃ በሚባለው በዛ በጴጥሮስ ስብከት 3000 ሰዎች አመኑ። እስጢፋኖስ የሚሉት ዲያቆን ሲገደል ተስፋ በመቁረጥ ፈንታ በዓለም ተበታትነው ወንጌልን አስተማሩ

**ንጉሥ፡-** በሁሉም ቦታ ሄዱ?

**አማካሪ 2 ፡-** አዎ

**ቀውላጦስ፡-** የሰናፍጭ ቅንጣት ወንጌል ስለተደቀሰች የአይሁድን፣ የአሕዛብን የክህደት አፍንጫ እየሰነፈጠች ግዛትዋን አስፋፋች። ከመካከለኛው ምሥራቅ ከኢየሩሳሌም እልፍ ፅንፍ እስከ ፅንፍ ደረሰች። ወደ አውስትርያ፣ እስክንድርያ፣ ኤፌሶን፣ ሲርምናስ፣ ኢትዮጵያ፣ አቴና፣ ቁስጥንጥንያ ተጓዘች፣ ተሰራጨች ከተባለስ ቆየ ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ ፡-** አንተም ይህንን ያህል ሰምተህል ቀውላጦስ?

**ቀውላጦሥ፡-** ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ፡-** ንጉሥ ሆይ ሲልኮ ማር ነው የሚዘንበው (እየሳቀ)

**አማካሪ 1 ፡-** የትልቅ ሰው ልጅ አይደል ለምዷል

**ንጉሥ፡-** በል ተናገር

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ (ተነሥቶ ወደ መድረክ ጠርዝ ቆም ብሎ በመመሰጥ) ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን ለሰው

ብሎ ምሕረትን ከምታሰጥ ከድንግል ማርያም በቤተልሔም ተወለደ፡፡ ሔሮድስ አሳደደው እንደገና ተመለሰ፤ ሐዋርያትን መረጠ፤ ሕሙማን ሥጋን በተአምራት የነፍስ በሽተኞችን በትምህርት አዳነ፡፡ በመጨረሻም የብርሃን ችቦ ማየት ባልወደዱ አይሁድ ተይዞ ለፍርድ ቀርበ ተሰቃየ፡፡ ለደቀ መዝሙሩ አደራውን ሰጠ፤ ፍጹም የድኅነቱን ሥራ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምልጃና ቅዱሳንን ሥልጣን ሰጠ ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ተቀበረ፤ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ ብሎ ባለፈው ቅዱስ ጴጥሮስ የሚሉት በአደባባይ ሲመሰክር ሰምቻለሁ፡፡

**ንጉሥ፡-** (በንዴት ከመቀመጫቸው ለመነሣት እየቃጡ ቆጣ ብለው) አንተ ይህን ያህል ሲናገር ሰምተህ ዝም ብለህ በልብህ ከመቅበር በሰይፍ አትሰይፈውም ነበር?

**አማካሪ 1፡-** ንጉሥ ሆይ አይናደዱ! እነሱ ሰው ተብለው ይናቁዋቸው፡፡

**ንጉሥ ፡-** ያም አለ ያም የሰላም ከተማ የተባለችውን በዮርዳኖስ ምዕራባዊ አቅጣጫ ከታላቁ ከተማ 50 ኪ.ሜ ርቃ በተራራማ ሀገር የምትገኘውን ኢየሩሳሌምን ወደ እስክንድርያ ብሎም በአጠቃላይ በአንዱ ግዛታችን ባሉ ክርስቲያኖች ላይ አንዳች አፋጣን ውሣኔ በቅርቡ መወሠን አለበት፡፡ አይመስላችሁም? (ሁለቱ አማካሪዎች ተነሥተው)

**አማካሪ 1 እና 2 ፡-** እውነት ነው ንጉሥ ሆይ

**አማካሪ 2 ፡-** (እንደቆመ) በእኛ ግዛት ያሉትስ አያመልጡንም ያች ፑንት ቶኤቶር ኩሽ አቢሲኒያ ወይም በአረቦች አጠራር ሀበሽ የተባለች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖችን እንዴት እናገኛቸዋለን?

**አማካሪ 1 ፡-** እነዛ ድሮም በኦሪት እግዚአብሔርን የሚያመልኩ አሁንም በጃንደረባው አማካኝነት የክርስቶስ መምጣት የተነገራቸው

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ እነርሱ ኃይለኛ ናቸው፡፡ ያ ኦሪት የሚባለው መጽሐፋቸው የሀገሪቱን የጆኦግራፊ አቀማመጥ፣ ወንዟን፣ አልማዟን፣ ወርቋን ብሎም የንግድ እንቅስቃሴዋን ሲገልጽ፤ የሕዝባቸውን ኃያልነት በተደጋጋሚ አንሥቶታል፡፡ እና እነሱን መነካካት በምን ልጥፋ ማለት ነው፡፡ የሀገራቸው ስም ራሱ ሀገረ እግዚአብሔር ነው የሚባለው፡፡ አምላካቸው በኩራት ‹‹የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?›› ብሏቸዋል፡፡ ብዙ የግሪክ ባለቅኔዎችና ጸሐፊዎች እነ ሆሜር ሄሮዳተስ እና ሌሎችም ስለኃያልነታቸውና ስለጸባያቸው ብዙ ብዙ ብለውላቸዋል፡፡

**ንጉሥ፡-** (በእርጋታ) ጥሩ ከዚሁ ከሮማ እንጀምራለን፡፡ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ወደ ማዶ እንሻገራለን፡፡ (ንጉሥ ከተቀመጡበት በመነሣት ትንሽ ተንጎራደው ካሰቡ በኂላ ወደ አማካሪዎች እየተመለከቱ) ታዲያ እነዚህን ክርስቲያኖች ለማጥፋት አሊያም ለእኛ እንዲሰግዱ ለማድረግ ምን ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?

**አማካሪ 1፡-** ከማንኛውም ማኅበራዊ ኑሮ ማግለል፣ ለሮማውያን የሚደረገውን እንክብካቤ ለእነሱ መንፈግ፣ አንድ ሮማዊ የሆነ ሁሉ ወንጀል ቢፈጽም እንኳን ሲመረመር በጅራፍ መገረፍ የለበትም፡፡ የሞት ፍርድ ቢፈረድበት ይሰየፍ እንጂ መሰቀል የለበትም ጥፋቱን ካመነ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ለእነዚህ ለክርስቲያኖች ግን ይህ መብት የላቸውም ንጉሥ ሆይ (ጭካኔ በተሞላበት 00000 መች ያ ብቻ ትንሽ ጥፋት እንዳጠፉ መግረፍ፣ ማንገላታት ብሎም እንደ አምላካቸው በመስቀል ነው ያኔ

**ንጉሡ፡-** (በንዴት) አዎ ያኔ አንገታቸውን ደፍተው ይሰግዱልናል፡፡ ተስፋቸው ይጨልማል፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ ክርስቲያኖች በንጉሥነትዎ ዙፋን በደልን የፈጸሙ አይደለም፡፡ መልካሙን ነገር ለመቀበል ፈጣን ናቸው፡፡ ተሰቅሎ የሞተላቸውን አምላካቸውን ከመውደዳቸው የተነሣ ሌላ አምላክ ፈጽሞ አይቀበሉም፡፡ ግፋ ቢል እስከ ሞት ይደርሳሉ እንጂ ታዲያ እንዲህ እየተባለ የሚነገርላቸው ሰዎች ይህ ውሣኔ ለንጉሥነትዎም የፍርድ ወንበር አይዛባብዎትም?

**ንጉሥ፡-** አያዛባም (በፍጥነት ከአፍ ነጥቀው) ደካማ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይልቅ ያልገባኝ ምሥጢር አለ፤ እነዚህ በእኛ ዘንድ ግምት ያልተሰጣቸው ሰዎች እስከሞት ራሳቸውን አሳልፈው ለመስጠት መዘጋጀታቸው ምን እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ተማምነው ይሆን?

**አማካሪ 1 ፡-** ምን አልባት ገንዘብ አላቸው ይሆን?

**አማካሪ 2፡-** የላቸውም መናጢ ደሀ ናቸው፤ ይልቅ ጉልበት እንዳላቸው?

**ንጉሥ፡-** ኡፍ! ድንቄም ጉልበት? ሲመቱ፣ ሲንገላቱ ዝም የሚሉ ደካሞች ናቸው! ደግሞ የእነሱ ጉልበት!

**ቀላውጦስ፡-** አይመስለኝም ሲተው እየተውት እንጂ ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ኃይል … በቃ በአጠቃላይ በብዙ ነገር ጠንካሮች ናቸው ነው የሚባልላቸው። አፍአዊ ጉልበት ሳይሆን መንፈሳዊ ውስጣዊ ኃይል ነው ያላቸው።

**ንጉሥ፡-** ውሸት ነው … ግን አንድ የሆነ ነገር መኖር አለበት እንዲህ ለመጣደፋቸው፣ ቀን ከሌሊት ለመትጋታቸው፣ ሀብት ንብረት ጥለው ለመመነናቸው።

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ አምላካቸው የዋዛ አይደለም። የሚጠራውና የሚውለው ከቀራጩ፣ ከዓሣ አጥማጁ፣ ከየኔቢጤው፣ ከበሽተኛው ጋር ነው። ታናሽነታቸውን አይንቅም። ያች ዘማዊ ማርያም እንተእፍረት አይሁድ የምኩራብ ሹማምንት ሲያዩዋት በንዴት እየተንዘፈዘፉ ቆሻሻ፣ ርጉም፣ ርኩስ የሚሏትን እርሱ ግን ስትመጣ ዝም አለ። ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኛውን የማይጠየፍ አምላክ በፍቅር ተቀበላት። ታዲያ እንዲህ ምሕረት የተደረገለት ሰው ኀዘንተኛውን ሲያጽናና፣ የተራበውን ሲያበላ፣ ድውያንን ሲፈውስ፣ ትዕቢተኛውን ሲገስጽ የተመለከቱ ክርስቲያኖች ዛሬ ያን ካዱ ሲባሉ በልባቸው የተጻፈው የአምላካቸው ፍቅር እንደጦር እየወጋ እንኳን ሊያስክዳቸው መከራውን በደስታ እንዲቀበሉት ኃይል ሆናቸው። ያ ነው ንጉሥ ሆይ ያልተረዱት ምሥጢር።

**ንጉሥ፡-** /እኔም ቁንጣን እስከሚይዘው አበላዋለው፣ ናላው እስኪዞር አጠጣዋለሁ። ቅቤው፣ ማሩ፣ ሥጋው ሞልቷል ተትረፍርፏል የሚቀረኝ ነገር ቢኖር ተአምር ማሳየት ነው፤/ ይልቅ የእነሱ አምላክ ሲወለድ በቤተልሔም በከብቶች በረት ሄሮድስ ሲያሳድደው የሚታገስ፣ ሲመታ የማያንገረ00000፣ ሲሰደብ ዝም ሲሰቀል ዝም የሚል ነው። እኔ ግን በእኔነቴ ሲመጡ በጠላትነት የመጣብኝን በበለጠ ጥቃት በቅጽበት ሳልበቀል የማልመለስ የጀግኖች ጀግና ክንደ ፈርጣማ ፍጡር ነኝ ተሳሳትኩ?

**አማካሪ 1፡-** እንዴት ተሁኖ ስህተት ማን እንደርስዎ

**አማካሪ 2፡-** መሬት ቁልብጭ ሰማይ ድፍት ቢል

**ቀውላጦስ፡-** አይመስለኝም እርስዎ ፍጡር ነኝ አሉ እርሱ ግን ፈጣሪ እንደሆነና የሰውን ልጅ ኃጢአት በደሙ እንዳነጻ፣ ቤተ ክርስቲያንንም በደሙ እንደመሠረተ፣ በክብር ተነሥቶ እንዳረገ፣ የኃያላን ኃያል፣ የጌቶች ጌታ፣ የንጉሦች ንጉሥ፣ ሥልጣኑ ጊዜ የማይሽረው እንደሆነ የሚታመን ነው።

**ንጉሥ፡-** አንተ ቀውላጦስ እኔ ከሹመትህ እንዳላወርድህ እነሱ የሚሉትን አትስማ! እንኳን አንተን እናቴንም…..

**አማካሪ 1 ፡-** (ንጉሥን ያቋርጣቸውና) እንዴ ንጉሥ እንደስዎ የሚሆን የለም ልጅነቱ ነው

**ንጉሥ፡-** ጥሩ አስተውለኸዋል (በእርጋታ) አማካሪ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ፡-** ፈጠን ብለህ የጦር መኮንኑን ጥራው (አማካሪ ሄዶ ይጠራል)

**መኳንንት 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ ሺ ዓመት ይንገሡ (በኅብረት)

**አማካሪ 1 እና 2፡-** እውነት ነው (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** ስሙ እየሰማችሁ ነው?

**መኳንንት 1 እና 2፡-** አዎ ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ፡-** ማንኛውም ወታደር የሚሳተፍበት ጥብቅ ትእዛዝ በሮማ ምድር ቀን ከሌት ተሯሩጣችሁ ክርስቲያን የሆኑትን አጥፏቸው፣ አሳዷቸው ይህችን ዓለም የአሕዛብ ዓለም አድርጓት። ወገባቸውን አደግድገው፣ አንገታቸውን ደፍተው፣ ለጥብለው ጉልበታቸውን አንበርክከው እስካልሰገዱልን ድረስ ውሣኔው የጸና ነው።

**መኳንንት 1 እና 2፡-** እሺ ንጉሥ ሆይ ቃልዎት በተግባር ይፈጸማል። (በኅብረት) (እጅ ነሥተው ሲወጡ)

**ንጉሥ፡-** ና.ና.ና ….

**መኮንን 2፡-** (ተነጥሎ ይመጣና) አቤት ንጉሥ ሺ ዓመት ይንገሡ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** እውነት ነው (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** የተፈጸመውን ማንኛውንም ድርጊት እንድታቀርቡ

**መኮንን 2፡-** ቃልዎ በተግባር ይፈጸማል (ልክ እንደወጣ)

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ ውሣኔው መልካም አልመሰለኝም

**ንጉሥ፡-** (ተነሥተው ለመሄድ እየተዘጋጁ) ካልመሰለህ አልመሰለህም ብዙ የማስተዳደር ልምዱ ያለኝ እኔ ነኝ። (ወጥተው ይሄዳሉ መጋረጃ ይዘጋል)

## ትእይንት ሦስት

(የንጉሡ ወንበር እንደተስተካከለ፣ የአማካሪዎችም በግራና በቀኝ እንዳለ፣ ጠረጴዛ ላይ የምግብ ትርፍራፊ፣ የተለያዩ መጠጦች ትርምስምስ ብሎ ከንጉሡ መቀመጫ ፊት አለ። ሠራተኛ ብቻዋን ዕቃ ልታሰናዳና ልታጸዳ ትመጣለች ምግቡን እያየች)

**ሠራተኛ፡-** ንጉሥ ጡንቻቸው የሚያብጠው፣ ድምፃቸው የሚጎረንነው፣ ዓይናቸው የሚፈጠው ይህን ምግብ ሲውጡ እየዋሉ ነወ ለካ! እኔ ኮ ምንድ ነው እንዲህ ቤት አላስገባቸው እስኪል የሚያሳድጋቸው እል ነበር። መኖር ጥሩ ብዙ ነገር ያሳያል። አሁንማ በየቀኑ እያበጡ ሲሄዱ እየፈራለሁላቸው ነው። አንዱ የጠላቸው ጎሽም ያደረጋቸው እንደሆነ ተሽረክ ብለው እንዳይፈርጡ፤ ያሰጋል ያሰጋል። (በማሾፍ) (ምግቡን ሁለት ጊዜ ጎርሳ አጣጠመችና መጠጡን ልትጠጣ ስታስጠጋው ዘበኛ 1 ይመጣል)

**ሠራተኛ፡-** (በድንጋጤ) ውይ አንተየ መጠጡ የተበላሸ መሆኑን ለማወቅ ሳሸተው መጣህ

**ዘበኛ 1፡-** ሴትና መላ አሉ! አትፍሪኝ ግን የእውነቱን ለማወቅ መናገር ጥሩ ነው። ይልቅ ሳትፈሪ አብረን እንብላ። (እየበሉ እያለ ዘበኛ 2 በመሐል ይመጣል)

**ዘበኛ 2፡-** ኧረ እየበሉ!

**ሠራተኛ፡-** (በማሾፍ) አንተዬ ልንጠራህ ስንል መጣህ (ሦስቱም በኅብረት ቶሎ ቶሎ ይበላሉ በመሐል ሠራተኛዋ ለዘበኛ 2 ልታጎርሰው እጇን ትዘረጋና አሳስታው ዘበኛ 1ን ታጎርሰዋለች)

**ዘበኛ 2፡-** አንቺ ታሳሽኛለሽ? ተልካሻ!

**ሠራተኛ፡-** አንተ ሞትም የቀደመውን ነው ይባላል። ደግሞ አሁን እኛን የማይገንቅ ከወታደር እርሱ (ወደ ዘበኛ 1 እየጠቆመች) ከጌቶች ቤተሰቦች እሌኒ፣ ከሹማምንቶች ቀውላጦስ ነው! አንተ እኔ ኮ ክብር ያለኝ ሰው ነኝ አላወከኝም እንዴ?

**ዘበኛ፡-** እህ ገና ለገና ከእበት ጠራጊነት ስለተጠራሽ

**ሠራተኛ፡-** እኮ ያን ማን ያገኘዋል። አንተዬ ጌቶች ከሚመገቡበት ቤት መግባት የሚበሉትን ማየት ኧረ ስንቱ

**ዘበኛ 2፡-** እሱማ ከማየትም አልፈሽ እየበላሽ አይደል

**ሠራተኛ፡-** ድሮም ካላዋቂ ሰው ጋር መነጋገር ይህ ነው ጥፋቱ

**ዘበኛ 2፡-** በይ በይ አበዛሽው ሕፃንን አጫውቶ አጫውቶ ዓይኑን ጠንቁሎ ማባረር ነው አሉ። (በንዴት ሊመታት ሲነሣ)

**ዘበኛ 1፡-** (እሱንና እሷን መሐል በመግባት እየገላገለ) አታፍርም ይህችን ተማተህ ጀግና ልትባል ነው

**ሠራተኛ፡-** ቆይማ ንጉሥ ሲመጡ ፊታቸው ላይ ባላቆምህ ልብ በልማ (ዘበኛ 2 ተናዶ እየፎከረ ወቶ ይሄዳል፤ ሠራተኛዋም ዕቃውን ሸካክፋ እያጉረመረመች ትወጣለች፤ ዘበኛ 1 የጥበቃ ሥራውን መድረኩ ጠርዝ ላይ ቆሞ ይሠራል፤ በመሐል እሌኒ ከውጭ ትገባለች)

**እሌኒ፡-** አፖሎ

**ዘበኛ፡-** አቤት የእኔ እመቤት! እ.... ልዕልት እሌኒ.... ስሜ ተቀይሯል።

**እሌኒ፡-** ማን ቀየረው?

**ዘበኛ፡-** ቀውላጦስ

**እሌኒ፡-** ለምን?

**ዘበኛ 1፡-** የግሪክ አማልክት እነ ጁፒተር የሰማይ ንግሥት፣ የሳቅ የፍቅር አምላክ እነ ቬነስ፣ የሲኦል አምላክ እነ ፑልቶ ሲሆኑ፣ የአንተ ስም አፖሎ የፀሐይ የመድኃኒት፣ የጨረቃና የግጥም አምላክ ነው ስለዚህ ስምህ ከእንግዲህ ወዲህ ሶምሶን ይባል አለኝ፡፡

**እሌኒ፡-** (እየሳቀች) በጣም! ጥሩ ለመሆኑ ክርስቲያኖች ከመጣባቸው መአት ማምለጫና መሸሸጊያ የጸሎት ቤት ወደሆነችው ግበበምድር ሄደህ አድርስልኝ ያልኩህን ምግብ አደረስክልኝ ?

**ዘበኛ 1፡-** አዎ እመቤቴ ግን በጣም ያሳዝናሉ፡፡ ዝናቡ፣ ፀሐዩ ከዛ በላይ ወታደሮች እየገረፉ እያሰሩዋቸው ነው እናትና ልጁ እየተጠፋፉ ሲያለቅስ በጣም ያሳዝናሉ፡፡ (ሁለቱም እንዳዘኑ ቀውላጦ ይመጣል)

**ቀውላጦስ፡-**ሶምሶን ደህና ነህ አንተ ደግሞ በዛው መማር ስትችል ጥለኸው መጣህ

**ዘበኛ 1፡-** ቶሎ ድረስ ስለተባልኩ እኮ ነው፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ምን አደረክ?

**ዘበኛ 1፡-** አንዱን ወታደር በዱላ አልኩት፡፡ በጣም ጨካኝ ነው በሰይፍ አንዱን አስተማሪ ሊገድለው ሲል.....

**ቀውላጦ፡-** በቃ ጉልቤ ሆንክ ማለት ነው፡፡ ሁሉን በጉልበት ነው በል ሂድ (ዘበኛ 1 እንደመሳቅ እያለ ወጥቶ ይሄዳል)

**እሌኒ፡-** ቀውላጦስ በተመሰቃቀለች ዓለም ውስጥ ገባሁ

**ቀውላጦስ፡-** ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ

**እሌኒ፡-** ንጉሥ ኔሮን ሀሳባቸውን ይቀይራሉ ተብሎ የተጠበቀው ተስፋ ማታ በጨለማ አንተ በሌለህበት ተሰብስበው እንደገና አጸኑ፤ በክርስቲያኖች ያለው በደል በዛው ይቀጥል ተባለ ሌላም....

**ቀውላጦስ፡-** (እያዘነ) ሌላ ደግሞ ምን

**እሌኒ፡-** ሌላው ደግሞ ባለፈው እኔን ለማግባት ሽር ጉድ ይል የነበረው የጋላስ ሹም ንጉሡን በእጅ በእግር ብሎ አሳምኗቸዋል ተባለ፡፡ በጣም ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ አንደኛ ሰውየውን ሳየው በጣም ጭካኔ የተሞላበት ነው፣ ሁለተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንዲነገረው የማይፈልግ ነው፣ ሦስተኛ በዚህ አሰቃቂ ጊዜ በእነሱ ሞት እኔ ሙሽራ ሆኜ ሊጨፈር፣ ሊበላ፣ ሊጠጣ.....

**ቀውላጦስ፡-** አስቸጋሪ ነው፡፡

**እሌኒ፡-** ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች የምረዳውን ገንዘብ ማን እንደነገረው ሳላውቅ እሺ ማለት አለብሽ እያለ እያንገራገረኝ ሰነበተ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ምርጫው የአንቺ ቢሆንም የሃይማኖት አንድነት በጥንቃቄ መርምሮ ማረጋገጥ፣ በዕድሜ፣ በጠባይ፣ በመንፈስና በአዕምሮ ተመጣጣኝ ደረጃ እንዲኖር ጥልቅ ጥናት ማድረግ እንደሚገባ እጠቁማለሁ፡፡

**እሌኒ፡-** እሱ እኮ ነው የተመሰቃቀለብኝ ነገር፡፡ እምቢ እንዳልል በንጉሥ ትእዛዝ ስር ነኝ፣ እንደገናም አጋልጣለሁ እያለ ይዝታል፡፡ እሺ እንዳልል የዘረዘርኩት ችግር አለ እና

**ቀውላጦስ፡-** እሌኒ ብዙ አያስጨንቅሽ መስቀሉን ለመሸከም ተዘጋጁ በውስጣቸው ግኖስቲኮች የተባሉ መናፍቃን እየበጠበጡዋቸው፣ በውጭ በንጉሥ ኔሮን ትእዛዝ የተላኩ ወታደሮች ስቃይ እየጨመሩባቸው በሄዱበት ጊዜ አንቺ ለሰማያዊው አስቢ ሁሉም ነገር አላፊ ጠፊ ነው እና በፈተና እንድትጸኚ ጸልዩ፡፡ ክርስቲያኖች በሚጸልዩበት፣ እርስ በእርስ በሚተሳሰቡበት በግበበ ምድር በጸሎት እንዲያስቡን እናገራለሁ

**እሌኒ፡-** በል እስኪ … ብቻ ነገሩ

**ቀውላጦስ ፡-** በተከበበበ ከተማ የሚያስደንቅ ምሕረቱን ለእኔ የገለጠ እግዚአብሔር ይመስገን እያለ ነቢዩ ዳዊት የዘመረውን መዝሙር ትዝ አይልሽም? አሁን ሁሉም ነገር የከበደን፣ የሚያስጨንቀን፣ የተከበብን፣ ሁሉ ነገር ከአቅማችን በላይ የሆነ ቢመስለንም ከእኛ ጋራ ያለው እግዚአብሔር ኢያሪኮን አፍርሶ ወደ ከነአን የሚያስገባን አምላክ ነው፡፡

**እሌኒ፡-** የመጨረሻውን ውጤት ማየት እናፍቃለሁ፡፡

**ቀውላጦስ ፡-** መቼም በክርስትና ጉዞ ሁል ጊዜ ደስታ የለም፡፡ ክርስትና የደስትና የመዝናናት መንገድ ቢኖረው ኖሮ ማንም መንግሥተ ሰማያት አይደርስም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሥጋዊ ደስታ ጥጋብን ያመነጫል፡፡ ጥጋብ ደግሞ

የጠብና የጦርነት ምንጭ ነው። ካልጠገቡ አይዘሉ ነውና ሰው ይጨርሳል መንገደኛ ያልቃል። መከራ የክርስቲያን ኃይል ነው ያጠነክራል። መከራ ከእንቅልፍ ያላቅቀዋል። ፈተና ሳይኖር ሰው ሁሉ እንደተኛ ምጽአት ይደርስበት ነበር።

**እሌኒ፡-** እሺ ቀውላጦስ በቶሎ ተመለስ፤ ከዛ ያሉ አባቶችን ሰላም በልልኝ፤ በጸሎታቸው እንዲያስቡኝ አደራ በላቸው።

(ቀውላጦስ ወጥቶ ይሄዳል፣ መዝሙር ይከፈታል። እሌኒ ተንበርክካ ትጸልያለች። በመሐል ተላላኪ ይገባል)

**ተላላኪ፡-** ምን እያደረግሽ ነው?

**እሌኒ፡-** (በድንጋጤና እልህ በተሞላበት አነጋገር) እየጸለይኩ

**ተላላኪ፡-** ተይ አልተባልሽም! አለዛ ለንጉሥ እንደሚነገራቸው አልተነገረሽም? ልዕልት እሌኒ አንዴ ከንጉሥ እጅ ከገባሽ በቶሎ እንደማትወጪ እወቂ። ክንዳቸው ያረፈበት ሰው በቶሎ ሲነሣ አላየሁም እና አስቢበት።

**እሌኒ፡-** ሰው ከደረሰበት መከራ የተለየ ከሰማይ አይወርድብኝ።

**ተላላኪ፡-** እኔ ምን ቸገረኝ ግን አንድ ቀን እናገራለሁ የግድ ነው ምክንያቱም ከንጉሥ አንቺን ስለማላቀርብ፤ ሌላው ሊያገባሽ የፈለገውን ሰውዬ እሺ እንድትዪው እለምንሻለሁ።

**እሌኒ፡-** (በመንገፍገፍ) አታፍርም! (መጋረጃ ይዘጋል)

## ትእይንት አራት

(መጋረጃ ሲከፈት የንጉሥ ወንበር ተስተካክሎ፣ የአማካሪዎች በዳርና በዳር፣ በአንድ ጎን እሌኒና ቀውላጦስ አንድ ላይ ቁጭ ብለው ዘበኞች የተለመደ ቦታቸውን መድረኩ ጠርዝና ጠርዝ እንደቆሙ የመድረክ መጋረጃ ይከፈታል። ሁለቱ መኳንንት ይገቡና እጅ ይነሣሉ)

**መኮንን 1፡-** ንጉ ሆይ አይመኑ ንጉ

**መከንን 2፡-** የታዘዝነውን በመፈጸም ላይ እንገኛለን

**ንጉሥ፡-** አደረጋችሁ!?

**መኮንን 1፡-** በሮማ ላይ የመጣውን ረሀብና ችግር ያመጡ የሮማን አማልክት ክርስቲያኖች በመናቃቸው ነው፤ ስለዚህ ንጉሥ እነሱ እንዲጠፉ አዝዟል በማለት ለሕዝብ አሳውቀን እንደ ንጋት ኮከብ የሚወረወሩት ወታደሮች ክርስቲያኖችን እያሳደዱ ግማሾችን እንደ አምላካቸው በመስቀል ሲሰቅሉ ሌሎችን ለተራብ አንበሳ ሲሰጡ እርስዎም እንዳሉት አንዳንዶቹን ሰም እየነከርን በአትክልት ቦታ በጨለማ እንዲያበሩ አደረግን

**መኮንን 2፡-** ሌሎች በመጋዝ ተሰነጠቁ ምትር ምትርትር ብሎ ሥጋቸው በሜዳ ተበተነ ለማምለጥ ቢቃጣቸውም ግዛታችን ሰፊ በመሆኑ በቶሎ መውጣት አልቻሉም። ድካምና ረሀብ ያንገላታቸው አረጋውያንና ሕፃናትን እየተሸከሙ የሚጓዙ ጉልበት የለሽ ክርስቲያኖችን አድነን ለመደቆስ ጊዜ አልፈጀብንም።

**መኮንን 1፡-** ግማሾቹ ወደ እስክንድርያ ሌሎች ወደ እስራኤል ለመጓዝ ብዙ ሞከሩ ይገርማችኋል ያ የሐዋርያት አለቃ የተባለው የዮና እና የአማና ልጅ ጴጥሮስ እርስዎ ሹማምንት በሚሰበሰቡበት ተጥራቤሌን በተባለ ከታላቁ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያስተምር 70 ዓመት የታመመውን ሰው በተአምር አስነሥቶ መሳፍንቶቻችንን ሳይቀር ያሳመነብን ጴጥሮስ ሮማን ለቆ እንዲሄድ የእኛ ከሀዲዎች የአግሊኖስና አግሬት ሚስቶች አስልከው ቢሰዱትም የሆነውን ሳናውቅ ከኦፒያም ጎዳና ራእይ አይቶ ነው አሉ ተመልሶ መጣ። እጁንም ሰጠን እኛም ክንዳቸው ፈርጣማ በሆኑ ታማኝ ባለሟሎችም እንዲሰቀል ትእዛዝ ስንሰጥ......

**መኳንንት 2፡-** እኔ አለ የሸመገለ ሰውነቱን እያፍታታ በኩራት እኔ እንደ ጌታዬ ልሰቀል አይገባኝም ይልቅ ቁልቁል ስቀሉኝ አለ እኛም ምንገዶን ፍቱኝ አትበለን እንጂ ይሄማ ጥሩ ነው ብለን ቁልቁል ሰቀልነው። በመጨረሻም በቫቲካን ኮረብታ ተቀበረ።

**ንጉሥ፡-** (በደስታ እየዘለለ) ደግ አደረጋችሁ ጀግንነት እንዲያ ነው። እነሱን ብሎ ትእቢተኛ ደግ ደግ አደራገችሁ ልባችን ሀሴት ለበሰ ቅቤ ጠጣ!

**አማካሪ 1፡-** ያ በአባቱ የሮማ ዜግነት ያለው የኦሪት ትምህርት ከገማልያል የተማረ፣ እስጢፋኖስ ሲወገር የወታደሮች ልብስ ጠባቂ የነበረ፣ የኋላ ኋላ በደማስቆ ተአምር አይቶ የተገላቢጦሽ ቀን ከሌት ደከመኝ ሳይል የተሰቀለውን የክርስቶስን ወንጌል ሲያስተምር የነበረ፣ 14 መጽሐፍ ጽፎ፣ ለእኛም ሀገር ለሮማ ሰዎች ብሎ የጻፈው ጳውሎስ የት ደረሰ?

**መኮንን 1፡-** እርሱ ያ ብርሃናተ ዓለም ጳውሎስ የሚሉት ከእስር ቤት ሁለት ዓመት ሲማቅቅ ኖሮ በአሁኑ አዋጅ የፊጥኝ ታስሮ ቀረበና በኦስቲያ መንገድ ተሰይፎ እዛው ተቀበረ፡፡

**ንጉሥ፡-** (በፈንጠዝያ ዘለው ይነሣሉ፣ ወደ እነሱ በመጠጋት) ምን ላድርግላችሁ ምን ትሻላችሁ ምን ትሸለሙ? የኢሳይያስን መጽሐፍ እየጠቀሰ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ሁሉ ለእኔ ይንበርከክ፣ ምላስም ሁሉ እኔን ያመስግን ብሏል ብሎ ለእኔ የሚንበረከከው ሕዝብ ጥርግ ጥርግርግ አድርጎ ያስወሰደብኝ በሥልጣኔ፣ በሀገሬ፣ በወገኔ፣ በሀብት በንብረቱ እንዳላዝዝ የገዥዎች ገዥ እንዳልሆን ያደረገኝ ተገደለ አላችሁ እሰየው! ጀግና ጀግንነት እንዲያ ነው እ አማካሪ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ ሆይ (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** ወዘልውጥ ሰው ይታየኛል? (መኳንንት ማርከው ያመጡት ክርስቲን ስላለ)

**መኮንን 1፡-** ወደ እርስዎ ካመጣነው ከክርስቲያኖች መካከል ግኖስቲኮችን የሚቃወምና በአንድ ወቅት መሪዎን አንተ የዲያብሎስ የበኩር ልጅ ነህ ያለ በሌላ ጊዜ ደግሞ በእነሱ አጠራር ቀሬንጦስ መናፍቅ ሲመጣ ልጆች እባካችሁ ከዚህ ቦታ እንራቅ እውነት ጠላት ቀሬንጦስ ወደ እኛ እየመጣ ነውና ብሎ የብዙዎችን ልብ በንቀት ያሳረረ ለእኛም ጋሬጣ የሆነብንን ዳግማዊ ፖሊካርፐስን ይዘን መጥተናል፡፡

**ንጉሥ፡-** አስገባው እንየው ይሄንን እኳለ ጎዶሎ (ይገባል)

**አማካሪ 1፡-** ስገድ እንጂ?

**አማካሪ 2፡-** አትሰግድም?

**እሌኒ፡-** እምቢ ብሎ አይደል ቀድሞውንስ የተያዘ አልፈልግም ካለስ

**ንጉሥ፡-** ዳግማዊ ፖሊካርፐስ ማለት አንተ ነህ? ፈጠን በልና ተንበርከክ ስገድ፣ የሮማ ሰው እንዲያምጽባችሁ እንደምታስተምር ቃል ግባ፣ ለሠራኸው ሥራ ተጸጸት

**ዳግማይ ፖሊካርፐስ፡-** ሁሉንም እቀበላለሁ፣ ምድራዊ ስቃይ አላፊ ነው፡፡ መሞትና ተገንዞ መቀበር ወደጉድጓድ መግባትም የጠሉ ሁሉ ይገቡበታል፡፡ ከመቃብር ማዶ ስለዘለዓለማዊ ኑሮ ለምድር መሰቃየት የግድ ነው፡፡ እናም ሰማያዊ አባቴን እስከመጨረስ አልክድም፡፡ ቤተ ክርስቲያኔንም ለጠላት ዓይኔ እያ አሳልፌ አልሰጣትም፡፡ ሲቀር ሁሉም ይቀራል እኔ አፈር ከገባሁ በኋላ የወደዳችኋትን አድርጓት፡፡

**ንጉሥ፡-** (በንዴት) አሰደባችሁኝ እኮ አሰደባችሁኝ ወይኔ እኔ ኔሮን!

(ቀውላጦስ ፖሊካርፐስን እየገፈተረ በቀስታ ያስወጣዋል)

**ንጉሥ፡-** (ወደ እሌኒ እያየ) እሌኒ በወታደሮች እንዲገደል ትእዛዝ ስጪ (እሌኒ ከፖሊካርፐስ ጋር ወጥታ ትሄዳለች)

**መኮንን 1፡-** ምን እንታዘዝ ንጉሥ ሆይ?

**ንጉሥ፡-** በመጀመሪያ ላደረጋችሁት ድንቅ ሥራ አማካሪ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ ሆይ (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** ለወታደሮች ወርቅ ካባ እንዲሠራላቸው፡፡

**አማካሪ 1 እና 2፡-** እንደቃልዎ ሁሉም ይፈጸማል፡፡ (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** ጥሩ ጥሩ ኧ…(ተረጋግተው) መኳንንት

**መኳንንት 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ ሆይ (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** ይህ ቤተ መንግሥታችን ጠባብ ነው ከተማዋም አሮጌ ሆናለች፤ እናም እኔ በቅርቡ ወደ ተራራማው ቦታ እሄዳለሁ ከተማዋን አቃጥሏት፡፡ ያኔ ሰፊ ቤተ መንግሥትና አዲስ ከተማ ይሠራልናል፡፡ ትእዛዙ ጥብቅ ነው፡፡

**መኳንንት 1 እና 2፡-** እሺ ንጉሥ ሆይ እንደቃልዎ ሁሉም ይፈጸማል፡፡ (በኅብረት)

(እሌኒ ትገባለች የኀዘን ፊት ተደቅኖባታል መኳንንት ትእዛዙን ተቀብለው ይወጣሉ)

**ቀውላጦስ፡-** ንጉሥ ሆይ አባቶች ደክመው የቆሮቆሩትንና ያቀኑትን ከተማ ማቃጠሉ ዕድገታችንን ከመግታቱም በላይ ወደ ኋላ አሽቀንጥሮ እንደሚሰደን አይዘንጉ፣ ሌላው ዕድሜ ልካችንን በጸጸትና በለቅሶ ልንተካው የማንችለውን የዘመዶቻችንን ነፍስ ይሞትብናል፡፡ ሌላው ደግሞ በክርስቲያኖች ላይ ግፍ እየበዛ ስለሆነ ቢቀነስ?

**ንጉሥ፡-** ለመሆኑ አንተ ማነህ? ደስ ሲለኝ ደስ የማይልህ አንተ ማነህ?

**ቀውላጦስ፡-** ቀውላጦ ነኝ፡፡

**ንጉሥ፡-** ስምህን መች አጣሁት?

**ቀውላጦስ፡-** ሰው ነኝ፡፡

**ንጉሥ፡-** ሰውማ ሰው ነህ ከእኛ መሐል አውሬ አለ ያለህ ማነው?

**ቀውላጦስ፡-** ማን ባዩ

**ንጉሥ፡-** በንዴት ይጮኽሉ፡፡

**ዘበኛ 1፡-** ንጉሥ ሆይ ምን አልባት እነዚህ የክርስቲያን ሴቶች ልዝብና ጭምት፣ ራሳቸውን የገዙ፣ ለወንድ የሚመቹ ስለሆኑ ምን አልባት…

**ንጉሥ፡-** አፍህን ዝጋ ደግሞ አንተ ከእኔ ጋር ልታወራ ፈለክ ወራዳ!

**አማካሪ 1፡-** ምንአልባት ለወደፊት ለማግባት ያቀዳት ካለች፡፡

**ንጉሥ፡-** (በንዴት) በሉ ሌላውን ወሬ ተውና ፈጠን ብላችሁ.....

(እሌኒ በፍጥነት መጥታ ጉልበታቸው ስር ተደፍታ ቀና ብላ)

**እሌኒ፡-** አባዬ … ቀውላጦስ ቶሎ የሚናደድ መሆኑን ከእኔ በላይ አንተ ታውቀዋለህ፡፡ ልጅ ነው ገና ምራቅ አልዋጠም፤ ደግሞ ይሄንን ዙፋን አልናቀም፡፡ ከልጅነት በመነጨ ሀሳብ ተንተርሶ በወጣትነት ካለው ትኩስ አመለካከት ጋር አጋጭቶ ተናገረ እንጂ ያለ እኮ ነው አባዬ ሰው ይሳሳታል፡፡ ደግሞ ንጉሥ የሚወደደው ሰዎች ሲያጠፉ ሲመክር ነው እንጂ፡፡

**ንጉሥ፡-** እሌኒ ከእሱ ጋር ምሥጢር እንዳለችሁ እየሰማሁ ነው፡፡ የዛሬ ሳምንት ልትዳሪ ስትዪ ታምሜአለሁ ብለሽ ሠርጉ ከወር በኋላ እንዲሆን አልሽ፤ ብዙ ወጭ ከወጣ በኋላም ሠርጉ እንዳይሆን አስቀረሽ፡፡ ሲያገባሽ የፈለገው ክቡር ባላባትም በነገሩ ስላላመነበት እሱንም ለማሳመን ብዙ ካሣ ከፍያለሁ አሁን ደግሞ.....

**እሌኒ፡-** እውነት ልናገር አባዬ

**ንጉሥ፡-** እኔ ምንም እንድትናገሪ አልፈልግም፡፡ ቀውላጦስን ከመግደል ምሬልሻለሁ፡፡ ለ2 ሳምንት እስር ቤት አስገቡት (ሲወስዱት መጋራጃው ይዘጋል)

## ትእይንት አምስት

(የዋሽንት ካሴት ይከፈታል ቀውላጦስ ፍራሹ ላይ (መሬት ላይ) ተኝቶ እሌኒ በሳህን ምግብ አምጥታ ታጎርሰዋለች)

**ዘበኛ1 ፡-** (ከውጭ እየገባ) ጋሻዬ እንደምን ዋልክ?

**ቀውላጦ፡-** (ድክምክም ባለ ድምፅ) እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ

**ዘበኛ፡-** ጋሻዬ አልተሻለህም ይህ ወህኒ ቤትኮ……

(በመሐል ቀውላጦስ የእሌኒን ጉርሻ እምቢ ይላታል አንገቱን ደግፋ )

**እሌኒ፡-** በእናትህ ቀውላጦ ብላ ካልበላህ አይሻልህም፡፡ አየህ አንተ ከዚህ ተኝተህ ቀረህ ማለት ብዙ ክርስቲያኖች መከራ ይበዛባቸዋል እና ለእነሱ ስትል እንኳን አንተነትህን የማቆየት አደራ አለብህ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ምን ላድርግ አልበላልኝ አለ፡፡ ምግቡ ትዝ አይለኝም… ለመሆኑ ያንቺ ሰውነት እንዴት ነው? ባል አላገባም በማለትሽ ተገርፈሻል ተባለ?

**እሌኒ፡-** ማነው ደግሞ ይሄን ያወራልህ፡፡ ሦስት ጊዜ ጀርባዬ ላይ ያረፈውንና በአራተኛ ቀኔ የተነሣሁትን እንደ መከራ መቀበል ተቆጥሮ ይናገራሉ? በጣም ባለጌዎች ናቸው አትንገሩት ብዬ ነበር፡፡

**እሌኒ፡-** አንተ ደግሞ (ወደ ዘበኛው ዞራ) እጅህ ለድብደባ ይፈጥናል፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ማንን ተማታ

**እሌኒ፡-** የሠራተኞችን እናቷ በእሳት ቃጠሎው ሞታባት ስታለቅስ ማልቀስ አይፈቀድም ብሎ ሊመታት ዘሎ ሄደ፡፡

(ቀውላጦስ ምርር ብሎ ያለቅሳል እሌኒ አንገቱን ቀና እያደረገችው)

**እሌኒ፡-** ቀውላጦስ አንተ፣ አንተን እኮ ነው፡፡

**ቀውላጦስ፡-** ተይኝ እባክሽ አውቃቸዋለሁ እኮ እንግዳ ተቀባይ፣ ለሐዋርያት ምግብ አዘጋጅ ደግ ሰው ነበሩ ባክሽ ተይኝ አልቅሼ ይውጣልኝ፡፡

**ዘበኛ 1፡-** /ነገሩ ከተሰማ ጋሻዬ ዓይኔ ብዙ ጉድ አየ ንጉሥ እንዳዘዙት የሮማ 2/3ኛው በእሳት ጋየ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን በእሳት ተለበለቡ ሀብት ንብረታቸው ጠፋ ሮማ ሀገራችን ለቅሶ በለቅሶ፣ ጩኸት በጩኸት ሆነች ያ መልካም መዓዛዋ በእሳት በተለበለቡ የሰዎች ሽታ ማለፊያ አሳጣች፡፡ ግማሽ ሰውነቱ የተቃጠለው እሪ ሲል፣ እናቱ የሞተችበት እዬዬ ሲል፣ የሚወዳት ሚስቱ አመድ ስትሆን እያየ የሚያደርገውን አጥቶ ሲቅበዘበዝ ይህም አልበቃ ብሎ ቃጠሎውን ያስነሡት ክርስቲያኖች ናቸው ተብሎ ሌላ ጥፋት በምእመን ላይ መጣ፡፡

**ቀውላጦስ፡-** አይ ዓለም፤ ዓለም በጣም አስቸጋሪ ናት (በመሐል ሠራተኛዋ ከጓዳ ትመጣለች)

**ሠራተኛ፡-** ጋሻዬ በየት ወጥቼ ልሂድ?

**ቀውላጦስ፡-** የት ነው የምትሄጂው?

**ሠራተኛ፡-** ከዛ

**ቀውላጦስ፡-** እኔ ራሴ እስረኛ ነኝ ማዘዝ አልችልም ገና የምፈታበት ቀን ሲደርስ

**ሠራተኛ፡-** መቼ ነው?

**ቀውላጦስ፡-** ከአራት ቀን በኋላ

**ሠራተኛ፡-** (ተክዛ ታለቅሳለች ከዛ ሁሉም ሆድ ይብሳቸውና ያለቅሳሉ) (ንጉሡ ከአማካሪዎቹ ጋር በደስታ እየተሳሳቁ ቀውላጦስ ከታሰረበት ቤት ሲመጡ ዘበኛ ያያቸውና)

**ዘበኛ 1፡-** ጋሻዬ ጋሻዬ ንጉሥ መጡ (ሠራተኛዋ ድንግጣ ወደ ጓዳዋ)

**ንጉሥ፡-** (በደስታ) ከተወለድኩ ጀምሮ እንዲህ ያለ ደስታ አላየሁም ዓይኔ ጉድ ነው ያየው፡፡

**አማካሪ 2፡-** እንዴ! የእሳቱ ወላፈን ሲንቦገቦግ፣ ጭሱ እየተትጎለጎለ ወደ ላይ ሲወጣ ሰማይና ምድር የተገለበጠች ነውኮ የመሰለው (በአድናቆት)

**አማካሪ 1፡-** በተለይ በአንዳንድ ቦታማ ቀስተ ደመና ነው የተከለው

**ንጉሥ፡-** ጩኸቱስ በተለይ የከብቱ፣ የጥጃው፣ የውሻው ኢ.ቤ.ት የሴቶች ድምፅ ቀጠን ብሎ ሲሰማ፣ ወንዱ ድምፅ በክርን እንደተደቆሰ ሲያስጓራው ... ኧረ ስንቱ ሩጫውስ ብትሉ አላያችሁትም መሰል? አንዷ ልጇን ይዛ ተፍ ተፍ ስትል ሲያቅታት ነፍሴ አውጭኝ ብላ ዞራ እያየች ልጇን ጥላ ስትሮጥ እንስሳቱና ሰው በአንድ ሲርመሰመስ ብቻ እያልፍ የለ አለፈ፡፡

**አማካሪ 2፡-** ግሩም ነው በጣም የሚያስደስት፡፡

**ንጉሥ፡-** በሉ ቶሎ ብላችሁ የሞቱትን ሰዎች ቅበሩና ከተማይቱን ጸድታ አዲስ ቤተ መንግሥትና አዲስ ከተማ፣ አዲስ ጣዖት እንዲሠራ ትእዛዝ አስተላልፉ፡፡ ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ አሉ፡፡

(በመሐል ሠራተኛዋ ከጓዳዋ ትወጣለች)

**ሠራተኛ፡-** ስሙ ንጉሥ ሆይ እናቴ ሙታ እርስዎ

**አማካሪ 1 ፡-** ዝም በይ ወራዳ

**ሠራተኛ፡-** እናንተ ቂሳሮች ዓይን እያላቸው የማያዩ፣ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ፣ እጅ እያላቸው የማይዳስሱ፣ አፍ እያላቸው የማናገሩ ግኡዛን ፍጥረቶች የሆኑትን ጣዖቶች ካላመለካችሁ ብላችሁ መአት አወረዳችሁ አይደል?

**አማካሪ 1 ፡-** (እየገፈተረ ሊያስወጣት እየሞከረ) ዝም አትይም

**እሌኒ፡-** ተዋት (በንዴት) ለምን አትናገርም፡፡ በድቅድቅ ጨለማ የበራው ብርሃን በልባችሁ እንዳይበራ ልባችሁ በትዕቢትና በሚያልፍ ሥልጣን ተመክቶ በላይ ብርሃን የበራላቸውን ለማጥፋት ሽርጉድ አላችሁ መች ያ ብቻ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ጥፋት ሳይገኝበት ሞተ የስርየት እንጂ የቅጣት ሞት ባይሆንም ቅሉ በመጀመሪያ በአይሁድ ሊቃነ ካህናት ጉባኤ በኂላም በሮም መንግሥት ተወካይ በጲላጦስ አደባባይ በዋለው ችሎት ይሙት በቃ ተፈርዶበት ሞተ፣ በመስቀል ላይ እንዲሰቀል አስደረጋችሁት፡፡ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ እንጂ በሮማ ወታደሮች አስጠበቃችሁት፡፡

**ሠራተኛ፡-** ከዚህ በኂላ የእርስዎ አሽከር መሆን አልፈልግም

**ንጉሡ፡-** (በንዴት እየተንዘፈዘፉ) አማካሪ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** (በፍጥነት) አቤት ንጉሥ ሆይ

**እሌኒ፡-** ይታገሱ! በልተው ሲጠግቡ ረሀብን፣ ሲበለጽጉ ድህነትንና ሌላውንም ይህን የመሳሰለውን መርሳት አልነበረብዎትም፡፡ ለሰውነትዎ የሚስፈልግዎትን ነገር ለማግኘት ማሰብ ሲችሉ ሰው በነፍሱና በሥጋው ጥፋት በገሀነም እሳት የሚቃጠልበትን መንገድ ለምን አዘጋጁ? ስለዚህ እግዚአብሔርን ይፍሩ በሥጋና በነፍስዎ ላይ ሥልጣን አለውና፡፡

**ንጉሥ፡-** ጨርሺው አንጀቴ እንዲቆርጥ ጨርሽው እንጂ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ የልጅነት ፍቅርሽን እንዲበጥሰው፡፡

**እሌኒ፡-** በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ እጅዎን አያንሡ፡፡ እንደ ኢዮርብአም እጅዎ ደርቃ ትቀራለችና የቤተ ክርስቲያንን ንዋየ ቅድሳት አያጥፉ፤ ለእርስዎም አይጠቀሙ እንደ ብልጣሶር በእግዚአብሔር ተመዝነው ቀለው ይገኛሉና፡፡ የእግዚአብሔርን ቤት አይዳፈሩ እንደ ኦዛ ይቀሰፋሉና፣ የሐሰት ምላስ ከአንደበትዎ አይውጣ እንደ ሐናና ሲጳራ ይዋረዳሉና ሁሉን ግን ፈጽመውታል ለፈጸሙት ለእያንዳንዱ ግን ንስሐ ባይገቡ አልሰማሁም እንዳይሉ ምላስዎን ለማሳፈር እንጂ

**ንጉሥ፡-** ያጎረስኩት ውሻ ነከሰኝ፣ አንጀቴን በእጥፍ ቆረጥሽው፣ እኔን የመሰለ አባት፣ እኔን የመሰለ አስተዋይ ሰው አጣሽ አንቺው በሳልሽ ሰይፍ ትሰየፊያለሽ አማካሪ

**አማካሪ 1 እና 2፡-** አቤት ንጉሥ (በኅብረት)

**ንጉሥ፡-** በሉ

**ቀውላጦስ፡-** (እየጮኸ) ንጉሥ ሆይ! ንጉሥ ሆይ! የፍርድ ቃል አይናገሩ በሴት ልጅ መፍረድ ጀግንነትዎን ይቀንስብዎታል፡፡

**ንጉሥ፡-** ምን?

**ቀውላጦስ፡-** እብድ ያውቃሉ እብድ? ልብስ የለበሰ፣ ያማረበት እብድ መልካሙን ሲያይ የነበረ ዓይን በመጋዝ የተሰነጠቁ በሰይፍ የተሰየፉ አካሎች ሲያይ፣ ጥሩ ዜማን መስማት የለመደ ጆሮ በጣር ላይ ያለን የሰለለን የሰው ድምፅ ጩኸትና ለቅሶ ሲሰማ፣ እጅም በበኩሉ ለመገነዝ ለማስታመም የሚያስቸግር አካል ሲገለብጥ፣ አፍንጫም የእሳት ቃጠሎ ውጤት የሆነን መጥፎ ጠረን ሲያሸት … ኸረ ስንቱ እና የነገሮችን ትስስር የሚያስተናግደው የሰው አዕምሮ ማሰብ ተስኖታል፡፡ እናም ሰዎች አብደዋል እነዚህ ይገደሉ ማለትዎ ተገቢ አይደለም፡፡

**አማካሪ 1፡-** ንጉሥ ሆይ ለማንኛውም ትንሽ እንመካከርበት (ሠራተኛዋና እሌኒ ወደ ውስጥ ይገባሉ)

**ንጉሥ፡-** ቀውላጦስ ወደ መጨረሻ የሕይወት ፍጻሜህ ተቃርበሀል፡፡ ለሁሉም ጥፋት ተጠያቂ አንተ ነህ

**ቀውላጦስ፡-** እኔም በበኩሌ ከአንገት በላይ ካልሆነ እውነቱን ልንገርዎትና ነፍሴ ሥራዎትን ትጠየፊዋለች፡፡

**አማካሪ 2፡-** ነው እኛ ለአንተ ጠበቃ እየሆንን አንተ?

**ንጉሥ፡-** ብያለሁ ብያለሁ ብያለሁ (ሰይፋቸውን መዘዙ)

**ቀውላጦስ፡-** (ከተኛበት ፍራሽ በቀስታ ይነሣል የዋሽንት ካሴት በቀስታ ይከፈታል) አብዛኛውን ዕድሜዬን ተቀጥሬ ያገለገልኩዎት ባለሚልዎት ነኝ፡፡ ንብረቴን አልያም የአገልግሎት ካሣዬን አልልም፡፡ ግን የእርስዎን የንዴት ሲቃ ያስታግስልኝ ዘንድ አምላኬን እለምነዋለሁ፡፡ በመጀመሪያ በክርስቶስ የተመሰረተችውን ኂላም በሰማዕታት ደም እየታነጸች ለአሕዛብ መብራት ለደከሙት ምርኩዝ፣ ለኃጢአተኞች ስርየትን የምትሰጠውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለሚመጣው ትውልድ አደራ እሰጣለሁ፡፡ ታሪክ ይመዘግበዋል፣ አንባቢ ያነበዋል፣ ልብ ያለው

በተግባር ይተረጉመዋል፡፡ አደራ የሚቀበል ክርስቲያን አደራውን ይወጣል፡፡ መድኃኔዓለም እንደተናገረ በስሜ ይመጣሉ የተባሉ እነ ሆድ አምላኮች፣ ምድራዊ አስተሳሰብ ያላቸው፣ ክርስቶስን ያለግብሩ ግብር ለሚሰጡ መለኮታዊ ባሕርይውን ለሚያሳንሱ ለወንጌል ሲሉ ደማቸው ያፈሰሱትን ቅዱሳንን ለሚንቁ፣ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የሆነችውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለሚያጥላሉ በአጠቃላይ ከእውነት መንገድ በመውጣት ከእውነተኛ ወንጌል በተሰበሰበበት የሐሰት ወንጌል ለማስተማር የዲያብሎስ ጋሻ ጃግሬ ለሆኑት ወዮታ ጥርስ ማፋጨት የማይጠፋ ታላቅ የማይበርድ እሳት የዘለዓለም ሞት እንዳለባቸው እናገራለሁ) አልሰማንም እንዳትሉ የቅዱሳን አፅም እሾህ ሆኖ እንዳይወጋቸው የሰማዕታት ደም በማዳን ፈንታ ማዕበል ሆኖ እንዳይወስዳቸው፣ የቅዱሳን እንባ በማማለድ ፈንታ እንዳያስፈርድባቸው ለሚመጣው ትውልድ ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቅ ዘንድ አደራ እላለሁ፡፡ በግበበ ምድር ያለ የክርስቲያኖች ኅብረት፣ ፍቅርና ትሕትና በየቤቱ ይደርስ ዘንድ ክርስቲያን ተለኩሶ እንደሚዳፈን የምድጃ ከሰል ሳይሆን ራሱ እያረረ ማእዛው እንደሚያውድ እንደ ዕጣን፣ ራሱን እያቀለጠ ብርሃን እንደሚሰጥ አንደ ሻማ፣ እሱ በዓለም ተጎሳቁሎ ለአሕዛብ ብርሃን ሊያበራ የሚችል የእግዚአብሔር ሰው መሆን አለበት፡፡ ንጉሥ ሆይ ለመጪው ትውልድ ይህን እንድናገር ጊዜ ስለሰጡኝ አመሰግንዎታለሁ፡፡ ፈቃድዎት ቢሆን የንስሐ ፍሬ ቢያፈሩ በዝናብ አብቅሎ የሚመግበውን ቸር ወደሆነ እግዚአብሔር ይንበረከኩ ዘንድ እማጸንዎታለሁ (ብሎ ዝቅ ሲል በሰይፍ ይሰይፉትና ይሞታል፡

**ንጉሥ፡-** (በንዴትና በእርጋታ) ደፋር! እንደ ባሕር አሸዋ የበዛውን ሠራዊቴን ሰብስብልኝ

(ዘበኛ 1 ሲቀር ሁሉም ይወጣሉ) (የዋሽንት ካሴት ይከፈታል)

**ዘበኛ 1፡-** እኔ አልመንንም ወንድሜን፣ አባቴን የገደለውን፣ ፍጹም ለእግዚአብሔር ልቡን ያንበረከከውን ኔሮንን ዛሬ አልያም ነገ የእነሱን ጽዋ እሰጠዋለሁ፡፡ (በጣም ያለቅሳል) (እያለቀሰ መጠነኛ ቀረርቶ ያቅራራል)

ያ ንፍጦ የሰነፍ ከርፋፋ
የሰይጣን ወዳጅ እጆቹ አዳፋ
እንኳን እያለ ተነጥቆ ቢሄድ በደመና
በመናፍስት ኃይል በአጀብ በዝና
ህቅ አድርጌው ህቅ ያድርገኝ ልጣል እስር ቤት
ለጊዜው ነዋሪ ነኝ የምኖር በኪራይ ቤት
ይልቅ አንድ ነገር ጥዬ አልፋለሁ ላለ ለቋሚ
ሰው የዘራውን እንደሚያጭድ አጥፊም ሆነ አልሚ
እናም ወደኋላ አልመለስም
ነፍሴ ከገነት ወጥታ ሲኦል ብትጠልቅም (እያለ ያለቅሳል)

(እሌኒና ሰራተኛዋ ከንዳ እየተላቀሱ በጩኸት ይመጡና መድረኩን ያደባልቁታል)

**እሌኒ፡-** ፍጹም ከአንተ መራቅ አልፈልግም ነበር ግን ከአቅም በላይ ሆነ ልትነጠለኝ ባትወድም ተነጠልከኝ ወንድምዬ (እያለች ታለቅሳለች) (መጋረጃው ይዘጋል)

***(ከመጋረጃው ውስጥ ዕብ 11፥35-38 ይነበባል)***

## ትእይንት ስድስት

(የሙሽራ ዓለማዊ ካሴት ይከፈታል፡፡ መድረኩ በአማካሪዎች፣ በመኳንንት፣ በዘበኞች ተሞልቶ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይጨፈራል፣ ድምቅምቅ ብሎ ይከፈታል) (የሙሽሪት የሠርግ ዋዜማ ነው) ዘበኛ 1 በቆመበት ተክዟል፣ ዘበኛ 2 በቆመበት ይጠጣል)

**አማካሪ 2፡-** በሉ ሁሉንም በመጠን እናድርግ

**አማካሪ 1፡-** የምን በመጠን ዛሬ ያልተዘፈነ ፣ዛሬ ያልተደለቀ ዛሬ ያልተበላ፣ ዛሬ ያልተጠጣ፣ ዛሬ ያልታየ እስክስታ …

**አማካሪ 2፡-** ማለቴ በጣም ብዙ ብዙ ነገር ስለሰማሁ ነው፡፡

**አማካሪ 1፡-** ዛሬውኑ የሚመጣውን እንጋፈጠዋለን፡፡

(ሁሉም በመቆም ይጨፍራሉ ዘበኛ 1 እንደፈዘዘ ነው)

**መኮንን 1 ፡-** (ወደ ዘበኛ 1 ዞሮ) ይሄ ዋዜማው ደምኖበታል፡፡

**አማካሪ 1፡-** ታሟል፣ ታሟል ሊያብድ ነው፡፡ (ንጉሡ ይመጣሉ ፈዘዋል) (ሁሉም በድንጋጤ ጸጥ ብለው እጅ ነሡ)

**ንጉሥ፡-** ይህች እሌኒ እያለቀሰች አስቸገረችኝ?

**አማካሪ 1 ፡-** ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ ወግ ነው ወግ ነው (በሰከረ አንደበት)

**ንጉሥ፡-** አይመስለኝም ከሰነበተ ጀምሮ እየየው ትላለች የማያልቅ እንባ ታነባለች፡፡

**አማካሪ 1 ፡-** ወግ ነው አልኮትኮ

**ንጉሥ፡-** ጥሩ ጥሩ እ… ከዚህ ብቻ አትቀመጡ እንጂ በየቦታው በየዝግጅቱ ዘወርወር ዘወርወር እያላችሁ ምን ጎደለ በሉ፡፡ ከየሀገሩ ግዛታችን የሚመጡ የሰቡ ፍሪዳዎች፣ ማር፣ ቅቤ ቶሎ ቶሎ እንዲጨመሩ ትእዛዝ ስጡ፡፡ (ብለው ንጉሡ ወጡ፡፡ አማካሪ 1 መስከር ጀምሯል፡፡ እየተንገዳገደ ወጣ ሁሉም ንጉሡን ተከትለው ወጡ ባዶ መድረክ ይሆናል በመሐል ሠራተኛዋ ትመጣለች)

**ሠራተኛ፡-** እንደው ከምኑ ልደብቃት ኧረ እንደው አንተ አውጣት (በመጨነቅና በማዘን) አዎ እንደውም ከዚህ ጭልል ካለው እንድትመጣ ለእመቤቴ ልንገራት (ብላ ዕቃውን አነሣሥታ ትሄዳለች)

(እሌኒ የሙሽርነት ልብስ ለብሳ መጣች፣ እቤት ውስጥ የተከፈተውን የሠርግ ካሴት ታጠፋና)

**እሌኒ፡-** ቅጥ ያጣ ሕይወት፣ በሥጋ ተድላ የተሸፈነች የቀጨጨች ነፍስ የተተበተበች መውጫ ያጣች በስቃይ ሕይወት እሷነቷን ያጣች ነፍስ ይዞ ጋብቻ (ወደ ሰማይ እያንጋጠጠች) (ዘበኛ 1 ገብቶ ከጀርባዋ ይቆማል) ጌታ ሆይ የሚያጽናናኝን ወስደህ፣ በአሕዛብ መካከል ተከብቤያለሁ የመኖር ትርጉሙ ባልገባቸው ምን ያህል በምድር እንደሚቆዩ ከሞት በኋላም ስላለው ሕይወት ባልተገነዘቡ በትእቢተኞችና በመጨካኞች መካከል በተዘጋጀ መድረክ ላይ ቆሜአለሁ፡፡ አባት ሆይ በእኔ አሻንጉሊት መጫወቻነት የራሳቸውን ደስታና ፈንጠዝያ ሲጫወቱ በቅዱሳን አጽም፣ በሰማዕታት ደም የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያን አደራ ሳልወጣ ወደማልፈልገው አዘቅት ልገባ ነው አደራሽ ድንግል ሆይ! ድረሽልኝ (ብላ መሬት ላይ ትደፋለች ‹‹አድኚኝ እናቴ›› የሚለው መዝሙር ይከፈታል) በሃይማኖት በምግባር ከማይመሳሰል ሰው ጋር ሦስት ጉልቻ እንዴት ይተከላል? ያውም በዚህ የሰማዕታት ዘመን፣ በክርስትና ጉዞ እውነትም በቂ ሰላምን አየር መተንፈስ አይቻልም፡፡ በአጀብ አጀብ ፍቅር ጋብቻ አይመሠረትም፡፡ የምን ማንቀላፋት የምን መተኛት፡፡ ሴት ብሆንም ስንት ሴቶች አሉ ለእምነታቸው ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ እና እኔም… (የሙሽራ ልብሷን ማወላለቅ ጀመረች) ዓለም እስከሆነች ሁሌ ጎደሎ ነች ሁሌ፡፡ ከንቱ ነች እና ሴትነቴ ከተጋድሎ ምዕራፍ አያግደኝም (ብላ ዘወር ስትል ዘበኛ 1 ቁሞ አየችው)

**እሌኒ፡-** ውይ

**ዘበኛ 1፡-** አይዞሽ የኔ እመቤት! አይዞሽ ተጋድሎውን በድፍረት ጀምሪ

**እሌኒ፡-** እሺ… ወደ ግበበምድር ለመሄድ ፈልጌ ነበር…

**ዘበኛ 1፡-** ጥሩ! በጣም ጥሩ! በመጀመሪያ ወደ ከተማው መውጫ ባለው ከዚህኛው በራፍ ውጭ ከዛ በዛፎች መካከል ባለችው ቀጭንና ቀጥ ባለችው መንገድ ሂጂ የንጉሥ መኳንንቶችና ወታደሮች ያን መንገድ አላስተዋሉትም ባለፈው ስትልኪኝ የምሄድባት ናት፡፡

**እሌኒ፡-** እኔንም ባለፈው ቀውላጦስ በዛ ወስዶኛል (በፍጥነት ቀሪ ልብሷን ልታወላልቅ ወደ ጓዳ ገብታ ቀይራ ትመጣለች)

**ዘበኛ 1፡-** በመጨረሻም ከክርስ መቃብር ሳትደርሺ በምሥራቅ አቅጣጫ ሂጂ፡፡ ፈጠን ፈጠን በይ ንጉሡና አማካሪዎቹ ወደዚህ ሳይዛወሩ (እሌኒ ወጥታ እሮጠች ትሄዳለች)

**ዘበኛ 1፡-** እኔም ከዚህ እስከመጨረሻው እታገላለሁ

**መኮንን 1፡-** (ከውጭ ይመጣል) ከዚህ የለችም (ብሎ ሲወጣ ሲል)

**ዘበኛ 1፡-** ና ና ና ማንን ፈለክ?

**መኮንን 1፡-** እሌኒን

**ዘበኛ 1 ፡-** ትመጣለች ተቀምጠህ ጠብቃት

**መኮንን 1፡-** ንጉሡ እየጠረጠሩ ነው (ንጉሡ እንደተናደዱ ይገባሉ)

**ንጉሥ፡-** የለችም?

**መኮንን 1፡-** የለችም፡፡

**ንጉሥ፡-** ከመኖሪያ ቦታዋ፣ ከመዝናኛ ቦታዋ፣ ከምትማርበት ክፍል፣ ነፋስ ከምትቀበልበት ክፍል … ከዚያ ከሌለች የት (አማካሪ 2 እየሮጠ ይገባል)

**አማካሪ 2፡-** ንጉሥ ሆይ! ንጉሥ ሆይ! (ከላይ ከላይ እየተነፈሰ) እሌኒ በጣም እየሮጠች ወደ ካታኮምቦ ሄደች አሉ፡፡

**ንጉሥ፡-** ፈጠን ፈጠን በሉ ወታደሮችን ላኩ ከዛ ከገባች አትያዘንም ሳትገባ እንድንይዛት ፈጠን በሉ (አማካሪ 2 እና መኮንን 1 በፍጥነት እየሮጡ ይሄዳሉ)

**ንጉሥ፡-** ዛሬ ዙፋኔን አዋረደችው፣ በትረ መንግሥቴን አስናቀችው፡፡ እነዛ መናጢዎች የሰጧት ልብ ወይኔ እኔ ኔሮን ክንዴ ሳይዝል (አማካሪ 1 በጣም ሰክሮ እየተንገዳገደ ይመጣል)

**አማካሪ 1፡-** አይዞዎት ንጉሥ የትም አትገባም፡፡ (እየተንገዳገደ) እኔ መዝፈን ነው ያማረኝ፡፡ (አሸሸው ገዳዬ አሃ ገዳዬ….)

**ንጉሥ፡-** (ወደ ዘበኛ 1 ዞሮ) ወታደር ሰይፉን አምጣ

**ዘበኛ 1፡-** ለምን ንጉሥ?

**ንጉሥ፡-** ቀርፋፋ! እየሰማህ ለምን ብለህ ትጠይቀኛለህ ያቺ ወጠጤ በእኔነቴ ነው የመጣችው፡፡ እንደመጣች እዚህ ላይ አንገቷን ስቀላው ታያለህ፡፡ በዙፋኔ እጇን ቀሰረች፣ ተዋርዳ አዋረደችኝ፣ ከእኔ ይልቅ ደካማ ክርስቲያኖችን ወደደች፤ ፈጠን በል!

**ዘበኛ 1፡-** ጨካኝ

**ንጉሥ፡-** ምን

**ዘበኛ 1፡-** ወሮበላ

**ንጉሥ፡-** እሰኪ ድገመው (እየተጠጉ)

**ዘበኛ 1፡-** ጨካኝ ወሮበላ (ንጉሥ በጣም ሲጠጉ ሰይፉን መዘዘ፤ ንጉሥ እየተንቀጠቀጡ በአማካሪ 1 ተደበቁ)

**ዘበኛ 1፡-** ተነግረህ ላትሰማ
ተለምነህ ላታቅማማ
የጫርከው እሳት
የጎመድከው እናት
አውጣው ዛሬ
ያን የጉማ አውሬ
ተንኮለኛ
የክርስቲያን ቀበኛ (እየፎከረ ሲጠጋቸው)

**ንጉሥ፡-** የዛሬን፣ የዛሬን፣ ኧረ የዛሬን

**አማካሪ 1፡-** አይንቦቅቦቁ እንጂ ንጉሥ! ኧረ ንጉሥ ፈሱ! (ብሎ ሲስቅ አማካሪ 2 በጀርባው ድንገት ይመጣና ዘበኛ 1ን በሰይፍ ይመታዋል ይሞታል፡፡)

**ንጉሥ፡-** (በመዝናናት) በቃ ጉሮሮውን ልተናነቀው ስል ነው የደረስከው፡፡ በፈረጠመው ጡንቻዬ ድባቅ ልመታው ስል ደረስክ በእጄ ነፍስ ሊጠፋ ነበር ቀደምከኝ፡፡

**አማካሪ 2፡-** የሆነ የቅዠት፣ የጩኸት ድምፅ ሰምቼ እየፈጠንኩ መጣሁ

**ንጉሥ፡-** ጩኸ፣ በቁሙ ተንቀጠቀጠ ይሄ ቀጣፊ ሰይፍ ቢይዝ የሚያሸንፍ መስሎት፣ ዓይኑን አፍጥጦ እንደነበር ጭንቅላቱ ላይ ልወጣበት ስል ተንበረከከ በሉ አስክሬኑን ከዛ ለዘመዶቹ ስጥ

**አማካሪ 2፡-** እሺ

**አማካሪ 1፡-** ንጉሥ ሆይ! ንጉሥ ሆይ! በተለያየ ቦታ ያለው ሰው በእርስዎ ላይ አምጿል አሉ፡፡ አሁን ከተለያዩ ቦታ የመጡ ሰዎች ጋር ስለዚህ ጉዳይ ነው ስንነጋገር የነበረው፡፡ እሌኒ ደግሞ ካታኮም ገብታለች፡፡

**ንጉሥ፡-** (ትንሽ ካሰቡ በኋላ የፌዝ ፈገግታ) ከጠላኝማ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ (ዝምታ) ነገሩማኮ ከቤት ነው የጀመረኝ ባበላሁ፣ ባጠጣሁ፣ ተንከባክቤ ባሳደኩ ዞረው በእኔ አመጹ፡፡ ጥሩ ከእንግዲህ በኋላ ነገ ጠዋት ጀምረን ሌላ ሀገር እንሄዳለን እና ዛሬውኑ ለጉዞ የሚሆን ማንኛውንም ነገር አዘጋጁ፡፡ ስንቅ፣ በቅሎ፣ ወታደር … ሁሉም ይዘጋጅ ፈጠን በሉ ማታም ስትሠሩ እደሩ እኔ እመጣለሁ፡፡

**አማካሪ 2፡-** እሺ ንጉሥ ሆይ

**ንጉሥ፡-** ምን እነ ቀበጤ (መጋረጃው ይዘጋል፡፡)

## ትእይንት ሰባት

(ንጉሡና ዘበኛ 2 ሲጓዙ ይቆዩና ንጉሡ ወገባቸውን ሊፈትሹ መጣሁ ብለው ቀርፋፋ ብለው ሰድበውት ይገባሉ፡፡)

**ዘበኛ 2፡-** (በጣም ተናዷል እየፎከረ ጠበቃቸው) ለብዙ ጊዜ ያገለገልኩ ታማኝ ዘበኛቸው ነበርኩ ዛሬ ግን …

እሳቸው ካልገደልኩ እኔ ሰላሜን አላገኝም (ብሎ እየጠበቃቸው እያለ ከሄዱበት ተመለሱ)

**ንጉሥ፡-** አንተ ደካማ ዘበኛ

**ዘበኛ 2፡-** አቤት ንጉሥ ምን አሉኝ?

**ንጉሥ፡-** ደካማ ቀርፋፋ (ሴፉን ይመዝዛል)

**ዘበኛ 2፡-** ምን? አረመኔ

**ንጉሥ፡-** (በጣም ፈርቶ) የዛሬን የዛሬን ተወኝ

**ዘበኛ 2፡-** ጨካኝ የምን የዛሬን መተው ነው፡፡ በነገሥክ በዓመትህ ደግ ሰው ነበርክ፡፡ ኋላ ግን በውስጥህ የደበቅከውን የአረመኔነት ባሕርይ ብቅ አደረግህ፡፡ የአባትህን ልጅ አስገደልክ፣ በ59 ዓ.ም እናትህን በመርዝ ገደልክ፣ በ61 ዓ.ም የልጅነት ሚስትህን ገደልክ፣ በ63 ዓ.ም እያስተማረ ያሳደገህ መምህርህን አስገደልክ፤ ያ አልበቃ ብሎ ደግሞ…… (ብሎ ይሰይፈዋል)

**ተፈጸመ**